# የጨረታ ማስታወቂያ

ወለጋ ዩኒቨርሲቲ በ2004 ዓ.ም በተያዘ በጀት ሁለት ጥልቅ የውኃ ጉድጓዶችን በሻምቡ ካምፓስ እና በጉድሩ የእንስሳት እርባታና ምርምር ማዕከል ወስጥ ለማስቆፈር ይፈልጋል፡፡

በዚሁ መሠረት፡

1. በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የጨረታ ሠነዱን ከወለጋ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ ከግዢ ንዑስ የሥራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 17 እና ከትምህርት ሚኒስቴር ቢሮ ቁጥር 322 በመቅረብ ለእያንዳንዱ የጨረታ ሠነድ የማይመለስ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) በመክፈል ለአንዱ ወይም ለሁለቱ የተዘጋጀውን የጨረታ ሠነድ ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ጥር 28ቀን 2004 ዓ.ም መግዛት ይችላሉ፡፡
2. የጨረታ ሠነዱን በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ እስከ ጥር 28ቀን 2004 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ወለጋ ዩኒቨርሲቲ ግዢ ንዑስ የሥራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 17 እና በትምህርት ሚኒስቴር ቢሮ ቁጥር 322 ለዚሁ ጨረታ በተዘጋጀው ሣጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
3. የጨረታ ሣጥን ጥር 28 ቀን 2004 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ ይዘጋል፡፡ የጨረታው ሣጥን በዚሁ ዕለት ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በግዢ ንዑስ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 17 እና በትምህርት ሚኒስቴር ቢሮ ቁጥር 322 የከፈታል፡፡
4. ጥር 28 ቀን 2004 ዓ.ም የሥራ ቀን ካልሆነ ቀጥሎ ባለው የሥራ ቀን ላይ ይሆናል፡፡
5. ተጨራቾች ከሚቀርቡት የጨረታ ሠነድ ጋር አካተው ማቅረብ ያለባቸው ሠነዶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

   ሀ. ለዘሙ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ የገንዘብ ሚኒስቴር የምዝገባ የምስክር ወረቀት

   ለ. ከፌደራል ሀገር ወስጥ ገቢ ወይም ከሌሎች ግብር ሰብሳቢ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ወቅታዊ የግብር ግዴታዎችን የተወጡና በጨረታው መካፈል የሚችሉ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ እና የሚጫረቱበት ዋጋ ከ100፣000.00 (መቶ ሺህ) ብር የሚበልጥ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ አለባቸው

   ሐ. የጨረታ ማስከበሪያ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለፀው መሰረት በባንክ በተረጋገጠ ቼክ (CPO) ከጨረታ ሠነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
6. ተጫራቾች የሚያስይዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ቢድ ቦንድ ማጠን በጨረታ መመሪያው ላይ የተገለጸ ሲሆን የቢድ ቦንድ አቀራረብም በባንክ በተረጋገጠ ቼክ /ሲፒኦ/ ከጨረታ ሠነዱ ጋር አሽገው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
7. ዩኒቨርሲቲው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የማሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

   ለማንኛውም ተጨማሪ ማብራሪያ ከዚህ በታች በተጠቀሱት አድራሻዎች ደውለው ማጠየቅ ይቻላል፡፡

   ስልክ ቁጥር፡- 0578619015/0578619050

<u>ወለጋ ዩኒቨርሲቲ</u>

<u>ነቀምቴ</u>

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional